የሰ/መ/ቁ.22007

22/6/98

ዳኞች፡- 1- አቶ መንበረፀሀይ ታደሠ

2- አቶ ዓብዱልቃድረ መሐመድ

3- አቶ ጌታቸው ምህረቱ

4- አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5- ወ/ት ሂሩት መለሰሠ

አመልካች፡- ወ/ት ቤትምወርቅ ጎሹ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አባያ መካኒካል ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ - ጠ/ኤልያስ ተ/ብርሃን

# ፍ ር ድ

በዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው ተጠሪ ያለምንም ምክንያት ከስራ ስላሠናበተኝ ህጉ የሚፈቅደው ክፍያ እንዲከፈለኝና የስራ ውሉ እንዲቋረጥ በማለት አመልካች በፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመሠረቱት ክስ ነው፡፡ ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤትም የስራ ውሉ ከህግ ውጪ የተቋረጠ በመሆኑ ተጠሪ ለአመልካች የተለያዩ ክፍያዎች በመፈፀም የሥራ ምስክር ወረቀት ሰጥቶ እንዲያሰናብታቸው ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሯል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበውም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በሠጠው ውሣኔ የህግ ስህተት በመፈፀሙ ስህተቱ እንዲታረም ነው፡፡ ችሎቱም በሥር ፍ/ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አኳያ የአመልካች ሥንብት ህገ ወጥ ነው? አይደለም?

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ______ ቀን 12-7-98

የሚለውን ለማጣራት መዝገቡ ለሠበር እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር ሠምቷል፡፡

አመልካች በክሣቸው የተከራከሩት ተጠሪ የአመት ፈቃድ ከሠጣቸው በኋላ በዛው ከስራ ያለበቂ ምክንያት አሠናብቶኛል በማለት ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የአመት ፈቃድ ከወሠዱ በኋላ ወደ ስራ ስላልተመለሱ የስራ ውሉ መቋረጡን ገልጿል፡፡

አመልካች የለበቂ ምክንያት ከሥራ ተሠናብቻለሁ ያሉ በመሆኑ ክሣቸውን የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካች ተጠሪ ለሠራተኞች የዓመት ፈቃድ የማይሠጥ መሆኑን፣ በድርጅቱ የተለመደ አሠራር የአመት ፈቃድ መስጠት የሠራተኛን የሥራ ውል ማቋረጫ መንገድ መሆኑንና፣ የሣቸውም የስራ ውል በዚሁ መሠረት መቋረጡን ባቀረቡት ምስክሮች አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች እንደ ክስ አቀራረባቸው ያስረዱ በመሆኑ በመከላከያ መልሱ ላይ የተገለፀውን ነገር የማስረዳት ሸክም ወደ ተጠሪ ይዞራል፡፡ ተጠሪ የሚከራከረው አመልካች የተፈቀደላቸውን የአመት እረፍት ከጨረሱ በኋላ ከሥራ ገበታቸው ቀርተዋል በማለት ቢሆንም ለምን ያህል ጊዜ የአመት ፈቃድ የተሠጣቸው መሆኑን፣ ይህ ጊዜ የሚያበቃው መቼ እንደነበረና ከተፈቀደላቸው ጊዜ በላይ ምን ያህል እንደቆዩ ያስረዳው ነገር የለም፡፡ እንደውም በሥር ፍ/ቤት ከመለሱ ጋር ያቀረበው ማስረጃ የሌለ መሆኑን ተመልክተናል፡፡

በፍ/ብሔር የሙግት ሥርዐት ደግሞ የሚታየው አቤቱታውን በተሻለ መልኩ ያስረዳው ማነው የሚለው ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እንደሚለው የሥራ መቋረጡ ምክንያት አመልካች ከተፈቀደላቸው ጊዜ በላይ ከሥራ ገበታቸው ላይ ለመገኘታቸው ጉዳይ ከሆነ ይህ ስለመሆኑ ማስረዳት የተጠሪ ሃላፊነት ነው፡፡ ሃላፊነቱን ግን አልተወጣም፡፡

… ጠቅላይ ፍርድ ቤት
… ግልባጭ
ፊርማ … ቀን 12-7-98

በአጠቃላይ ተጠሪ አመልካችን ያለማስጠንቀቂያ ለማሠናበት በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀፅ 27 ሥር ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ወይም ሌላኛው መኖሩን ማረጋገጥ መቻል አለበት። ይህን ማስረዳት ካልተቻለ ስንብቱ ህገ-ወጥ ይሆናል። በተያዘው ጉዳይ አመልካች የአዋጅን አንቀፅ 27/1/ለ/ እንደተመለከተው ከሥራ ገበታቸው ቀርተዋል በማለት ይከራከር እንጂ አባባሉን የሚያስረዳለት አንድም ማስረጃ አላቀረበም። ይህም የሚያሣየው ተጠሪ የአመልካችን የሥራ ውል ያቋረጠው ህጉ ከሚፈቅድለት ውጪ መሆኑን ነው። ስለሆነም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት በሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት መፈፀሙን ተረድተናል።

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1- የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.37928 ጥቅምት 29/1998 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።

2- የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.06573 የካቲት 4/1997 የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል።

3- ወጪና ኪሣራቸውን ግራ ቀኙ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል። ለመ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ወ.ፊ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 12-7-98